**March 27, 2009**

# ከስህተቱ የማይመር በታሪክ ተጠያቂ ነው!

የኢትዮጵያ ሕዝብ በእስር፣ በአፈናና በግድያ ልሳኑ ቢዘጋም በውጭ አገር ያለነው በአብዛኛችን የዕለት ተዕለት በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተጠምደን ስንገኝ፣ ሌላው ሆድ አደር ግን "የአባትህ አገር ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" እዳሉት በስመ ኢንቨስትመንት የግል ጥቅምን በማሳደድ የወያኔን ፖለቲካ ደጋፊ በመሆን፤ የቀረውም ፖለቲካን እንደ ጦር በመፍራት ኢትዮጵያን ለመለስ ዜናዊ ዘረኛ አስተዳደር እርግፍ አድርጎ በመተው ድንበሯ ተቆርሶ ለባዕድ ሲሰጥ፥ ሉአላዊነቷ ተደፍሮ፥ ንጹህን ልጆቿ በሆነና ባልሆኑ ምክንያቶች ለሞትና ለእሥራት እንዲሁም ለስደት እየተዳረጉ ናቸው።

እንዳለፈው ምርጫ የግድያ ዘመን በውጭ ሆነ በውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ በቅንጅት አመራር ውስጥ ተፈጥሮ በነበረው ክፍፍል ተስፋ በመቁረጡ ትግላዊ ተሳትፎው አመርቂ ባይመስልም፤ በተፈጠረው የፖለቲካ ክስረት አትራፊዎቹ ወያኔና ተለጣፊ ወዳጆቹ ናቸው። ወያኔን እያጠናከረ ያለው የእኛው ፖለቲከኞች "የእኔ መንገድ ብቻ" የሚሉ ግትሮችና ኢትዮጵያዊነት እየጠፋ ባለበት ወቅት ሥልጣን የሚጠማን ሆዳሞች ነን። አቶ መለስ ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ደደቢት በረሃ እንዳለ ከአልባኒያ ኮሙኒስት ታጋይነት እንደ ወቅቱ ነፋስ በቅጽበት ወደ ነፃ ገቢያ ኢኮኖሚ ተቀየርኩ ሲልና ምዕራባውያንን አታሎ ከለንደን ታጅቦ አዲስ አበባ ሲገባ እኛ ግን እውነትን ይዘን ለኢትዮጵያ እድገት ትግላችን ሰምሮልን በሕብረት ለቆመም እስካሁን አልቻልንም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋነኛ ጠላት ወያኔ/ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መሆኑን ምናልባት ተቃዋሚዎች ስላልተረዳን ይሁን ሌላ? በትግል በመጠላለፍ ላይ ተጣምደን ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ይታገል የነበረው "የትግራይ ነፃ አውጪ" የሆነው ሕ.ወ.ሐ.ት በአዲስ አበባ ከመንገሱም በላይ እርስ በርስ እያናከሰን ይገኛል። ያለፍንበት ሥርዓት ታሪክ ሆኖ መመቀመጥ ሲገባው፤ ነገር ግን አንዱ ዘር ጭቋኝ፤ ሌላው ዘር ተጨቋኝ፤ ሕ.ወ.ሐ.ት ከትግራይ አልፎ "የተጨቋኝ ነፃ አውጪ" በመምሰል ብዙሐን መገናኛ እየተጠቀመ አንዱ ዘር ከሌላው ዘር፥ አንዱ ሐይማኖት ከሌላው ተከባብሮ እንዳልኖር ሁሉ መርዝ እየረጨና እያጋደለን ይገኛል።

ሌላው ነገር የተቃዋሚ ጎራ ድክመቶችን መዳሰሱ ወያኔ እንደ ሚያደርገው ችግሮችን ቆስቁሶ አንዱን በሌላው ላይ ጣት ለማጠነቋቆል ሳይሆን ከስህተታችን ትምሕርት ይገኝ ይሆን በማለት ነው። እንደ ምሳሌም ቅንጅትን ብንወስድ በመሠረቱ አራት ቅንጅትን የመሰረቱ ድርጅቶች (ኢ.ዴ.ፓ/መድኅን፥ ኢ.ዲ.ሊ. ፥ ቀስተ ደመና ና መ.ኢ.አ.ድ) በጥልቀት ተወያይተውና ፕሮግራማቸውንም አብላልተው፥ ልዩነታቸውንና አንድነታቸውን ተማምነው መቻቻልን አዳብረው በውስጣቸው ያለውን የሥልጣን ጥማት ቆርጠው ቅንጅትን የፈጠሩ ሳይሆን የይድረስ ይድረስ ቅንብር በመሆኑና በተለይም ሁለት ካባ ለባሹ አቶ ልደቱ አያሌው በቅንጅቱ ውስጥ ተሰግስጎ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ለወያኔ አሳልፎ በመስጠቱና ታማኝነቱን ለወያኔ ለማብሰር ከውሕደት ሰነዱ ላይ አልፈርምም በማለቱ ቅንጅት ድርጅታዊ ሕጋዊነት እንዳያጣ በመገደዱና እንዲሁም በጥራት፥ በብቃትና በጥንካሬም መቀናጀት ባለመቻሉ በቀላሉ ለመከፋፈል በቃ። የወያኔ ተጽዕኖም ተደምሮበት ቅንጅት በመከፋፈሉ በርካታ አባላትና ደጋፊዎችን ተስፋ ከማስቆረጡም በላይ የተቃዋሚውን ኃይል ከፋፍሎታል።

እነዚህና የመሳሰሉም ስህተቶች አሁን ባለንበት የትግል ደረጃ ላይ የጣሉን ቢሆኑም፥ የብዙ ኢትዮጵያውያን ተስፋ መቁረጥና ተሳትፎ መቀነስ ያስከተለ ከመሆኑም በላይ ከትግሉ የሸሹና ለተወሰኑ ኢትዮጵያውያን የትግል ኃላፊነቱን የጣሉ ብዙዎች አሉ። ያለ መስዋዕትነት ድልን የምንፈልግም ብዙዎችም አለን።

የተቃዋሚዎች የትግል ስልተ ሂደታችን ሊለያይ ይችላል። ነገር ግን ግባችን ወያኔን ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቅላት ማውረድ ነው። የጋራ ትግላዊ ቅንብርም ኃይል ነው። ተቃዋሚ ፓርቲዎች አንድ ይሁኑ ማለትም አይደለም። ልዩነታቸው እንዳለ ሆኖ፤ አንድ በሚያደርጉን አገራዊ ጉዳዮች ላይ ተባብረውና ተቻችለው ለመሥራት ቅድሚያ መስጠት አለባቸው ማለት ነው። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ማለት ይህ ነው።

በየትኛውም የዓለም ታሪክ ውስጥ የአንድ አገር ዲሞክራሲያዊ ሆነ አምባገነናዊ መሪ የአገሩን መሬት ቆርሶ ለጎረቤት ሲሰጥ የታየበት አገር በታሪክ ውስጥ የለም። አቶ መለስ ግን አዲስ አበባን ወያኔ ከረገጠበት ቀን ጀምሮ ኤርትራን ገንጥሉልኝ በማለት ለተባበሩ መንግሥታት በቡትሮስ ጋሊ ዘመን ማመልከቻ ያገባ ሰው ነበር።

1ኛ/ የኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠልን በመደገፍ የኢትዮጵያ ህዝብ ሐብት ንብረት የሆነውን የአሰብን ወደብ አሳልፎ በመስጠት ኢትዮጵያን ባሕረ አልባ አድርጓታል።

2ኛ/ በባድሜ ጦርነት ከሰማኒያ ሽህ በላይ ኢትዮጵያውያን ሕወታቸውን ሰውተው ነገር ግን በአልጀርሱ ስምምነት አቶ መለስ ዜናዊ የባድሜ መሬት ለኤርትራ ይገባል ብሎ ፈርሞ ሰጥቷል። ዛሬ የኢትዮጵያውያንና የዓለም ሕዝብ ትክክለኛ መረጃ እንዳያገኙ እውነታን ከተጨባጭ በመነጠል የወያኔ ባለሥልጣናትና የመገናኛ ብዙሐን እያሰራጩ የሚገኙት ይህን ደባ ሽፈና ነው።

3ኛ/ ባለፉት ሥርዓቶች ሁሉ ኢትዮጵያ በጎረቤት አገሮች ተፈርታ ድንበሮቿ ተከብሮ የኖረች አገር ነበረች። ዛሬ ግን ወያኔ ደደቢት በረሃ ሆኖ ኢትዮጵያን ለማጥፋት ባወጣው ፕሮግራሙና ለሱዳን መንግሥት የገባውን ቃል ለማክበር የወያኔ ተቃዋሚ ኃይሎች ሱዳንን እንደ መግቢያ በር እንዳይጠቀሙ በማሰብ ለሱዳን መንግሥት እንደ ገጸ በረከት መሬታችንን ማለት ከሰሜን ጀምሮ እስከ ደቡብ 1600 ኪ/ሜ ርዝመትና በጥልቀት 50-60 ኪ/ሜ አሳልፎ ሰጥቷል። ወያኔ ከደደቢት ተራራ ሥር ወጥቶ ያደረገው ጥፋት ፋሽስት ጣሊያን ከአውሮፓ መጥቶ ካደረሰብን ጥፋት በልጦ ተገኝቷል።

ያለአማራጭ ሐሳብ ወቀሳን ብቻ በተቃዋሚዎች ላይ ሰንዝሮ ማላፉ አግባብና ገንቢም ስላልሆነ ምን መደረግ አለበት? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የኢትዮጵያን ሉአላዊነትዋነቷንና በአንድነቷንም የምናምን ልጆቿ ችግራችንን ለመፍታት ተቀራርበን መነጋገር ሆነ መደራደር አማራጭ የሌለው መፍትሔ ሲሆን፤ እስካሁን ድረስ የድርጅት መሪዎች ልዩነት በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ችግሮች ላይ ያተኮረ ሳይሆን ፖለቲካን የግል ንብረት በማስመሰል የእኔ ብቻ መደመጥ አለበት በማለት ላለመደራደር በመረጡ መሪዎች አቋም ምክንያት የተቃዋሚው ፖለቲካ አድሮ ቃሪያ፤ ታጥቦ ጭቃ፤ ሆኖ የወያኔ መሳለቂያ ሆነናል። ትግሉ ቅድሚያ መስጠት ያለበትም ለሥልጣን ሹክቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ነፃነት በጋራ መሻት ነበር። መተኮርም ያለበት አንድነታችንን እያፈረሰ ባለው በወያኔ መግሥት ላይ በጋራ መነሳት ብቻ ነው። አሁንም የትግል ስልታችን መሆን ያለበትም፥

1ኛ. የወያኔን ሥርዓት ጥፋቶች ከሰብአዊ መብት ረገጣ እስከ አገር መሸጥና ኢትዮጵያዊነትን ማጥፋት እንደ ጎጂነቱ ቅደም ተከተል በመስጠት ሥርዓቱን ለመገርሰስ የሚያግዱን፥ ወያኔ እኛን ለማጋጨት የሚጠቀምባቸውና በውስጣችን የተፈጠሩና የሚፈጠሩ ቅራኔዎችንና ልዩነቶችን ማጥበብ፣

2ኛ. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሁሉ ኢትዮጵያ ከወደቀችበት ችግር በጋራ ለማላቀቅ በምንችለው መንገድ የትግል አስተዋጽዖ ማድረግ የዜግነት ግዴታው መሆኑን አምኖ በመቀበል እራሱን ማሳመን። እስካሁን ድረስ የተወሰኑ ግለሰቦች ሆኑ ግሩፖች ለፖለቲካ ችግራችን መፍትሔ ያመጣሉ ተብሎ የታመነው ፈሊጥ አመርቂ ባይሆንም ለአገራችን በሐቀኝነት፥ በተጠያቂነት፥ በቁጭትና መስዋዕትነትን ለመክፈል በቆራጥነት መነሳት፥ መሪዎች ከስህተት መማርና ያለፈ

ስህተትን ያለመድገም፥ ትልቅ ችግር እያለ በትንሽ ነገር ላይ ያለማትኮር፣ በዓላማ ጽናትና በቆራጥነት መቆም ይፈለግባቸዋል።

3ኛ. አመለካከታችን ከሰፈርና ከጎሳ ወጣ ብሎ በኢትዮጵያዊነት ላይ ያተኮረ ሆኖ፤ በምድሯ ስንፈጠር ዘርን በምርጫ የወሰድነው ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠን ጸጋ በመሆኑ በመወለድ እትብታችን ከኢትዮጵያ አፈር በመቀበሩ ከአፈሯ በመቀላቀላችን በእኛነታችን ኮርተን በአንድነት ላይ የተመሰረተ ልዩነታንን አምነን የኢትዮጵያ ዜጎች በምድሯ የበቀልን አበባዎች እንደ መሆናችን መጠን ጎሳን ተከትሎ የሚመጡ እንቅፋቶችን ማጥበብና ማስወገድ። የሰው ዘር መገኛ በመሆናችን ለብዙ ዘመናት በሰላም አብረን ኖረናል ። ወደፊትም አብረን እንኖራለን። ከአንገት በላይ ሳይሆን በመሰረታዊ የሰው መብት እኩልነት እናምናለን።

4ኛ. በግለሰብ ደረጃ እንኳ በተቃራኒ ኃሳብ ብቻ እራስን አስታጥቆ የሌላውን ኃሳብ ላለመቀበል እራስን ያለማዘጋጀት፣ በማፍረስ ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብ ብቻ ላይ ያለመታነጽ፤ ነገሮችንም በቀናነት ማንሸራሸር መቻል፣ ሚዛናዊ መሆን፥ አሉባልታና ክፋትን ማስወገድ፤ ያለፈና የነበረን ጥፋት ይቅር ማለትን መቻል፣ መቻቻልን መልመድ፣ ወደፊት ለሚደረጉና የሚያቀራርቡን ገንቢ ሐሳቦችን ማፍለቅ።

5ኛ. ከወያኔ በመወገን የኢትዮጵያ ሕዝብን ጥቅም በመጉዳት የንብረት ባለቤት ለመሆን ለጊዜያዊ ጥቅም መሯሯጡ ትግልን መሸጥ መሆኑን ተረድተን ከድርጊቱ በመቆጠብ፤ ወደፊት የኢትዮጵያ መንግሥት ተመስርቶ የሕግ የበላይነት ሲሰፍን ለታለመው ንብረት ባለቤት መሆን የምንችል መሆናችንን ማመን።

6ኛ. ለ17 ዓመታት በወያኔ አገዛዝ ሥር መኖራችን የጥፋት ዘመን መሆኑን ተረድተን በጋራ ለመታገል ሕዝባዊ አመጽ በወያኔ መንግሥት ላይ ለማንሰራራት እራሰ መዘጋጀትና ከጎረቤት አገር ከኬንያ በመማር የወያኔ ሥርዓት ይብቃን ማለት። ወያኔን ለመጣል የሚያስፈልገን መሣሪያ ሳይሆን የተቀነባበረና በሕዝብ የተደገፈ አመጽ ስለሆነ መነሳትና ማነሳሳትን መቻል ።

በእነዚህና በሌሎችንም ችግሮች ተፈትኖ ከድርጅት ትግል አልፎ አገርን ለመምራት የሚቻለው አመራሩ በዲሞክራሲያዊ ሂደት ታንጾ የኢትዮጵያን ሕዝብ ፖለቲካዊ ትርታ ማዳመጥ መቻል ሲቻል ብቻ ነው። አንድ ፓርቲ ከሕዝብ ልብ ገብቶ ከጊዜው ፖለቲካ አብሮ መራመድ ለመቻሉ ሕዝቡ ምስክሩ ለመሆኑ እራሱን በራሱ መገምገም አለበት። እስካሁን ምን ሠራሁ? በሕዝቡስ ዘንድ ተቀባይነታችን ምን ያህል ነው? ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ እስካለለው ድረስ በስመ ተቃዋሚ የወረቀ ላይ ብቻ የመሆኑ በተገላቢጦሽ የወያኔን ጎራ ስለሚያጠናክር ፈተናን የማያልፉ ሁሉ ሕዝባዊ ተቀባይነት ስለሚጎላቸው ከድርጊታቸው ቢቆጠቡ የተቃዋሚው ጎራ ሊጠናከር ይችላል። ትግሉም ይሰምራል።

ከደመላሽ ካሣ
ካሊፎርኒያ